# የቪቶሪዮ ኦርላንዶዋ ጣልያን ዕጣ-ፈንታ በአማራ ላይ እንዳይደገም!!!

የአማራ ህዝብ ያለፍላጎቱ ጦርነት ተከፍቶበታል፣ ጦርነት ውስጥም ተማግዷል። እርግጥ ነው የጊዜ ጉዳይ እንጂ ሀገሪቱ ወደጦርነት እንደምታመራ ግልጽ ነበር። ከዚህ በፊት ደጋግመን እንደተናገርነው ፥ በሀገር አቀፍም ይሁን በዓለም አቀፍ የፖለቲካ አሰላለፍ ውስጥ፥ በ rising power (በኢትዮጵያ ሁኔታ ኦሮሙማ/ኦህዴድ) እና በ ruling/established power (ወያኔ-ትግሬ) መካከል የሚደረግ ፍትግያ ሁለቱን ሀይሎች "የቱሳይዳይድ ቅርቃር" (Thucydides Trap) ውስጥ እንደሚያስገባቸው እሙን ነው። ከዚህ ቅርቃር መውጣት የሚቻለው አንድም ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት እንግሊዝ አቅሟንና ልኳን አውቃ global power የሚለው ቦታዋን ለአሜሪካ በሰላም አስረክባ ገሸሽ እንዳለችው በሰላማዊ ሽግግር ይፈታል፥ አልያም ጀርመንና እንግሊዝ ለ14 ዓመታት ሲካረሩና ገመድ ሲጓተቱ ቆይተው በመጨረሻ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነትን እንዳስነሱት ወደጦርነት ተገብቶ በሀይል ይፈታል። የዚያች ሀገር ጉዳይም ከገባበት "የቱሳይዳይድ-ቅርቃር" ለመውጣት ሁለተኛውን መንገድ በይፋ ጀምሯል።

አማራ የእኔ የሚለው መንግሥት ስለሌለው፣ ራሱን አግልሎ ለመቆምም ይሁን በራሱ የጊዜ ሰሌዳ በሀይልም ቢሆን ርስቱን የማስመለስ ዕድል እንዳይኖረው በመደረጉ በወያኔ-ትግሬ ትንኮሳም ይሁን፥ በብአዴን ለአብይ አህመድ ሰጋጅነት፥ የዚህ ጦርነት አካል መሆኑ አይቀርም ነበር፤ ያም ሆኖ እያየነው ነው።

ከትናንት ማታ ጀምሮ የትግሬ አክቲቪስቶች፥ አማራን "ወንድሞቻችን ናችሁ" እያሉን ያሉት፥ ደም መፋሰስን ጠልተው ከመሰለን ስህተት ነው። ግማሽ ክፍለ ዘመን ደማችንን ሲያፈስሱ መኖራቸውንም ዘንግተው አይምሰልህ።
ተወደደም ተጠላ የዚህ የጦርነት game-changer የአማራ ህዝብ መሆኑን በደንብ ስለተገነዘቡት ነው። ያንን ደግሞ የበሻሻው "ንጉስ" የኦሮሙማው መሪ አብይ አህመድም ያውቀዋል።

አብይ አህመድ ግን አማራን በብአዴን በኩል እንዴት መጋለብ እንደሚችል ጠንቅቆ ስለሚያውቅ፥ የፈረሱን ጀርባ ልክ ስለሚያውቅ፥ "እውር ቢሸፍት ከጓሮ አያልፍም" ከሚል እብሪትም፣ ህዝባችንም የኦሮሙማን መንግስትና የብአዴንን ተላላኪነት ለከትየለሽነት በበቂ ካለመመርመር በስሜት እንደሚነዳ ስለሚያውቅ፥ አብይ የጦርነቱን ዓላማ ያለምንም ማቅማማት በሬድዋን ሁሴን በኩል በግልፅ ነግሮናል። ሬድዋን ሁሴን ትናንት የወታደራዊው ምክርቤት ቃል አቀባይ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ነበር የጦርነቱ ሶስት አላማዎች በሚል በዝርዝር እንደሚከተለው ያስቀመጠው፡-

1. ትግራይን ነፃ ማውጣት፣
2. ህገመንግስቱን ማስከበርና ማስረፅ፣
3. የሀገሪቱን አንድነት ማስጠበቅ።

ከላይ የተጠቀሱት ናቸው የፌደራል መንግሥቱ (የኦሮሙማው መንግሥት) አላማ።
በሌላ በኩል የአብይ መንግስት የጦርነት አላማ የአማራን የግዛት ጥያቄ የሚመልስ አድርገው የሚቀሰቅሱ በገሃድም ይሁን በጭምብል ያሉ ብአዴናዊያንን በሰፊው እየተመለከትን ነው። የእነዚህ መሰሪዎች ቅስቀሳ፥ አማራን በስሜት ለመኮርኮርና የአብይን አላማ ለማስፈፀም እንጂ የአማራን ርስት ለማስመለስ አይደለም። ነገ ወያኔ-ትግሬ በተወገደ ማግስት አብይ አህመድ የአማራ ሚሊሻንና የአማራ ልዩ ሀይልን፥ አሁን "አማራ ክልል" ወደሚባለው ድንበር ተመለሱ ሲል፥ ከአብይ ጎን ተሰልፈው፥ "ለቁራጭ መሬት ብለን ከትግራይ ህዝብ ጋር አንጋጭም፤ ችግራችን ህወሃት ነበር" ብለው፥ በዚህ ጦርነት የጥይት እራት የሚሆነውን የአማራ ወጣት ደም ተረማምደው አማራን የሚሸጡት እነዚህ ሰዎች ናቸው።

በሌላ በኩል፥ የተወሰዱ የአማራ ርስቶችን በተመለከተ "የጋራ ኮሚቴ እናቋቁም" ብለው የሆኑ ቡድኖች በተንቀሳቀሱበት ወቅት፥ አንድ ግለሰብ ለሚዲያ ተናግሮት የነበረው ዘገባ እንደሚያመለክተው፥ በተናጠል የተደረገ ስምምነት ያለና ከዚያ ባፈነገጠ መልኩ የሚደረግ የጋራ አቋም፥ "ባደረግነው ስምምነት ላይ ድጋፍ የሰጡን ኦሮሞዎች ጋር ስለሚያጋጨን የተናጠል አካሄድ መሄድ ይሻላል" የሚል ይዘት ያለው ነገር ተናግረው ነበር። እንግዲህ የተባለው አይነት ምስጢራዊ ስምምነት ኖረም አልኖረ ወይም ከላይ የጠቀስናቸው የብአዴን ቡችሎች የህዝብን ስሜት ለመኮርኮር በየፌስቡኩ እገሌን ለማስመለስ የሚል ሀሳዊ ስብከታቸው የአማራን ርስት ለማስመለስና ወሰን ለማስከበር ማሰሪያ (binding) ዋስትና አይሆንም።

ሲጀመር አብይ አህመድም ሆነ ስልጣኑን የተቆጣጠረው የኦሮሙማ ሀይል ፈፅሞ የማይታመንና ስነልቦናዊ ውቅሩ ራሱ utilitarian ነው። ተጠቅሞ የሚጥልህ፣ተሻግሮብህ ሲያበቃ፥ "ድልድይን ይሻገሩበታል እንጂ፥ ተሸክመውት አይሄዱም" ብሎ የሚተርትብህ ነው። አብይ አህመድ የሊላይ ገብረማርያም ቡድንንና በአዲስ አበባ የሚገኙ አንዳንድ የትግሬ ባለሀብቶችን ሰብስቦ እኮ "በትግራይ territorial integrity ላይ አንደራደርም ዋስትናም እንሰጣችኋለን" ያለ ሰው ነው።

ስለዚህ ወደ መፍትሔ ሀሳብ ከመሄዳችን በፊት ጥንቃቄ ካልተደረገ አማራ እንደ ቪቶሪዮ ኦርላንዶዋ ጣልያን እንዳይሆን ስጋቴን ላስቀድም።

===== አማራ እንደ ቪቶሪዮ ኦርላንዶዋ ጣልያን???? ======

ጣልያን እ.አ.አ ከ1896 ጀምሮ ከጀርመንና ከኦስትሮ-ሀንጋሪ ጋር የጦርነት ጥቃትን በጋራ ለመከላከል ውል ተፈራርማ ነበር።

በ1914 የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ሲጀምር ግን ጣሊያን "ገለልተኛ" ነኝ ስትል አወጀች። በ1915 ደግሞ በተለምዶ "የለንደን ስምምነት" የሚል ምስጢራዊ ውል ራሽያ፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ ካሉበት "የተባበሩት ሀይሎች" ከሚባሉት ጋር ተፈራረመች። ይህ የለንደን ውል፥ ጣልያን ከራሽያ፣ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ ጎን ቆማ ጀርመን፣ኦቶማን ቱርክንና ኦስትሮ-ሀንጋሪን ከወጋች፥ በድል ማግስት የሚከተሉት 10

ነገሮች እንደሚፈፀሙላት ቃል የሚገባ ውል ነበር፦

1. በብሬነር መሻገሪያ እስከ አልፓይን ውሃ ያለውን የኦስትሪያ አካል የሆነውን የታይሮል ግዛትን፣

2. በወቅቱ የኦስትሪያ አካል የነበረውን ኢስትሪያን ጨምሮ እስከ ትሪስተ ወደብ እንዲሁም የከረስ-ሎሺ አርኪፔላጎን፣

3. ዛድራና ሴቤንኮን ጨምሮ ሰሜን ዳልማሺያን እንዲሁም አብዛኛው የዳልማሺያን ደሴቶችን፣

4. በወቅቱ በኦስትሪያ ስር የካርኒዮላ ግዛት ስር የነበሩ ዛሬ የስሎቬኒያ ግዛት አካል የሆኑት ቪፓኮ፣ ኢድርያ እና ቢስቴርዛን፣

5. በኦስትሮ-ሀንጋሪ ስር የነበሩ ነገር ግን ጣልያኖች በብዛት የሚኖሩባቸው የፖንቴባ እና ማልቦርጌቶ ቫልቡርና ከተሞችን፣

6. በደቡባዊ የኤጂያን ባህር የሚገኙ የዛሬዋ ግሪክ አካል የሆኑ የዶድካኔዝ ደሴቶችን፣

7. የአልቤንያን የቬሎና ወደብ፣

8. አልቤኒያ ሉዓላዊነቷ ለጣልያን ተላልፎ እንደሚሰጥና ማንኛውንም የውጭ ግንኙነት ማድረግ የምትችለው በጣሊያን በኩል እንደሚሆን፣

9. የጀርመን የአፍሪካ ቅኝ ግዛቶችን መካፈል፣

10. የኦቶማን ቱርክ ኢምፓየር ሲፈርስ፥ በአንታሊያ በኩል ያለውን የሜዲትራንያን ባህር ክፍል መውሰድ፣

ከላይ የተጠቀሱትን ግዛቶች ለጣልያን እንደሚሰጥ ቃል የሚገባ ውል በምስጢር ተፈራርማ ነበር ጣልያን ጦርነቱን የተቀላቀለችው።

ለዚህ ጦርነት 450 ሺህ ልጆቿን ለሞት ገብራ 640 ሺህ ልጆቿን ቁስለኛ አድርጋ በኢኮኖሚ ተንኮታኩታ ስታበቃ፥ በድሉ ማግስት በተራ ቁጥር አንድ ላይ ከተጠቀሰው የታይሮል ግዛት ውስጥ በብዛት ጣልያኖች ከሚኖሩበት ቦታ በቀር "አፍንጫሽን ላሺ" ስትባል ለመፅናኛ በሊግ ኦፍ ኔሽንስ ውስጥ ቋሚ ወንበርና፥ የጦርነቱ ተሸናፊ ጀርመን ለአሸናፊዎች ካሳ እንድትከፍል ከተወሰነባት ገንዘብ ውስጥ ተቆንጥሮ ተወርውሮላታል።

የጠቅላይ ሚንስትር ቪቶሪዮ ኦርላንዶና የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሲድኒ ሶኒኖ ኢጣሊያ ከመጋረጃ ጀርባ ያደረገችው "የለንደን ውል" ውጤቱ፥ መካድና "አፍንጫህን ላስ" መባል ነው። በነገራችን ላይ ለቤኒቶ ሙሶሊኒ መነሳትም ምክንያት የሆነው ይህ ብሔራዊ ውርደት ነው።

* እንግዲህ ውል ስትፈፅም፥ ውሉ እንዲፀናና እንዲተገበር በራስ መቆም፣ የመካድ ዕጣ ፈንታ እንዳይገጥምህ አሳሪና እጅ ጠምዛዥ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ ይኖርብሃል። ይህንን የምለው የምናወራው የአማራ ህዝብ ለዘመናት ደም ስለገበረበት የርስት ጉዳይ ያገባናል፥ አዎ አጀንዳችን እሱና እሱ ነው የምንል ከሆነ ነው።

* ብአዴን እንደሆነ አብይ አህመድ ወደስልጣን በመጣ ማግስት ሁሉንም ወንበር በኦሮሞ ሲያስወርር፥ እንዴት እንዲህ ይሆናል? እንዴት ዝም ትላላችሁ? ሲባል፥ "እኛ የታገልነው ለስልጣን አይደለም" የሚል የከፍለ ዘመኑን የድንቁርና ቀልድ የቀለደ ጉድ ነው። በእርግጥ በኋላ ላይ "ቁዘማ ውስጥ ነኝ" እስከማለት አድርሶታል።

ነገም፥ አይ ወደጦርነት የአማራን ህዝብ ያስገባነው ከላይ ሬድዋን የጠቀሳቸውን ነጥቦች ለማስፈፀም እንጂ የአማራን ርስት ለማስመለስ አይደለም ማለቱ አይቀርም። ለዚህ ነው፥ ስለአማራ ቆሜአለሁ የሚል የፖለቲካ ሀይልም ይሁን ህዝባችን፥ የጦርነቱን ውጤት የሚወስነው የአማራ ተሳትፎ መሆኑን ከግምት አስገብቶ፥ የርስቶቻችንን ዘለቄታዊ ምልሰት ለማፅናት የሚበጅ እጅ ጠምዛዥ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ያለበት። አለበለዚያ ትግሬን "ነፃ ለማውጣት" አልያም አማራን እንደህዝብ የፈረጀን ህገመንግስት "ትግሬ እንዲያከብረው" ለማድረግ በሚል የኦሮሙማን ስልጣን ለማፅናት አማራ ልጆቹን cannon fodder (የጥይት እራት?) ማድረጉ ትርጉም አልባ ነው።

ወያኔ-ትግሬ የአማራ የምንጊዜም ጠላት ነው። መጥፋትም ያለበት ቡድን ነው። ከዚህ በላይ ግን የርስቶቻችን ጉዳይ የአማራ ህዝብ የዘመናት ጥያቄዎች ናቸው። በስመ ወያኔን ማጥፋት፥ ለአብይ ስልጣን የጥይት እራት ከሆንን በኋላ፥ የሊላይና የአብርሃም በላይን የትግራይ ብልፅግና በማንገስ፥ የአማራ ሚሊሻና የአማራ ልዩ ሀይል ከያዛቸውና ከሚይዛቸው በሀይል ከተነጠቁ ታሪካዊ የአማራ ርስቶቻችን ላይ ቀኝ ኋላ ዞር ተብሎ እንዳይመለስ ዛሬ ላይ ወጥሮ መስራት በእኔ በኩል የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው የሚል እምነት አለኝ።

"ዛሬ እዚህ ደርሰናል እዚያ ደርሰናል" የሚሉ ጩኸትና ፉከራዎች ቋሚ ዋስትናና ለርስቶቻችን መመለስ ማረጋገጫዎች አይደሉም። ዛሬማ መቀሌ ገብተህ የወያኔን ባንድራ ብታቃጥልለት፥ አብይ አህመድ ደስተኛ ነው፤ "ጀግናዬ፣ ታሪክ ሲዘክርህ የሚኖር" እያለ ሊያወድስህ ይችላል። ቁምነገሩ ግን፥ ወያኔ የሚባል መርዝን ደምና አጥንትህን ገብረህ ነቅለህ ስታበቃ፥ ብአዴንና መርዘኛ ካድሬዎቹ ያለምንም ማሰሪያና እጅ ጠምዛዥ ቅድመ ሁኔታ "ርስትህ ተመለሰ" እያሉ ስሜትህን ኮርኩረው ወደጦርነት እሳት ማግደውህ ካበቁ በኋላ፥ ነገ የአብይ አላማ ተፈፅሟል ቀኝ ኋላ ዞር ቢሉ ዋስትናው ምንድነው? መሰራት ካለበት መሰራት

ያለበት በዚህ ጉዳይ ነው!!!

ዛሬ የወያኔን ጠላትነት ሊነግረን የሚነሳው እኮ፥ ትናንት አማራን በአዳራሽ ሰብስቦ፥ ወያኔ-ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ የፈፀመውን ጅምላ የዘር ፍጅት "ማረጋገጫ ማስረጃ የለም" ሲል የነበረ ከሃዲ "ሰው መሳይ በሸንጎ" ሁሉ ነው። የወያኔ-ትግሬ መኖር ለአማራ መከራ ነው፤ ከዚያ እኩል ደግሞ የአማራ ታሪካዊ ርስቶችም መልስ ማግኘት ያለባቸው አሁን ነው። አማራም ሳይወድ ለተማገደበት ጦርነት ፥ ዋጋ ለመክፈል በአሳሪ ህዝባዊና ይፋ ውል ስርዓቱን ማሰር ያለበት በዚህ ቅድመ ሁኔታ ብቻ መሆን አለበት።

አለበለዚያ "በመከላከያ" ተብዬው ውስጥ ያለ የኦሮሞ ወታደር በትግሬ ድንጋያማ ተራራ ላይ ለአብይ ስልጣን ሲል ዋጋ እንደማይከፍል ግልጽ ነው።

ብአዴን ለአብይ ሎሌነት ስላደረ፥ በሬድዋን የተዘረዘረውን ግልፅ አላማ ለማስፈፀም፥ ቱሪናፋ ካድሬዎቹን እያስጮኸ፥ እንዲያውም "ከለንደን ውል" በከፋ ሁኔታ ምንም ማሰሪያ ዋስትና በሌለበት አማራን አነካክቶታል። ያገባኛል የሚል የአማራ የፖለቲካ ሀይል ካለ፥ መስራት ያለበት፥ የአማራ መስዋዕትነት ርስትን በማስመለስ ረገድ ማረጋገጫ የተመታለት እጅ ጠምዛዥ ነገር በማንበር ነው።

ከዚያ ውጪ ቀጣይ የአማራ ዕጣ ፈንታ ለአብይ አህመድ ስልጣን ማስጠበቂያ ደሙንና አጥንቱን ገብሮ ሲያበቃ እንደ ኦርላንዶዋ ጣልያን "ድልድይን ይሻገሩበታል እንጂ፥ ተሸክመውት አይሄዱም" ይሉት ብሂል ተተርቶበት፥ የአብርሃም በላይ የትግራይ ብልፅግናና "ከአለውሃ እስከወልቃይት የትግራይ ነው" እያለ ሲያቀረሽ የነበረው በባለሀብቶችና በምሁራን የተዋቀረው የሊላይ ገብረማርያም ቡድን አዲሱ ዘር የትግሬ ኢምፓየር በአማራ ግዛቶች ላይ እንዲሰፍን አድርጎ፥ ባዶ እጁን አጨብጭቦ መቅረቱ ነው።

ከስሜት ፥ ስሌት ይቅደም። ስሌት ሲቀድም የጦርነቱ ትሩፋትና ዋስትናው ላይ አጥብቀህ ትሰራለህ።

ፈጣሪ የአማራን ህዝብ ይጠብቅ!!!

ዴቭ ዳዊት።

06/11/2020